ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ጥቅምት 2001 ዓ.ም. **የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች** ቁጥር 19

# የልጆች ሕይወት በኢትዮጵያ

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

❋❋❋

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡

❋❋❋

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡

❋❋❋

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል፡፡

❋❋❋

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## መግቢያ

ኢትዮጵያን ጨምሮ በሁሉም የዓለም አገሮች ልጆችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸው የእነሱን ሕይወት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ሊነኩ የሚችሉ ፕሮጀክቶች የሚዘረጉት ስለ ልጆች ፍላጎት፣ ለምሳሌም ምን እንደሚወዱ ምን እንደሚፈልጉ እና እንደማይፈልጉ፣ በሕይወታቸውም ለምን ጉዳይ ቅድሚያ እንደሚሰጡ በደምብ በማይታወቅበት ሁኔታ ነው፡፡ ከሰው ልጆች ሁሉ ልጆችን ነጥለን ብንመለከት ስለ እነሱ አጠቃላይ ሕይወት የሚዘረዝሩ ጥናቶችና የጽሁፍ መረጃዎችን አናሳ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከዚህ ቀደም ልጆችን በተመለከተ የተጻፉትን እና በፖሊሲ የተቀረጹትን ነገሮች ስንመለከት ደግሞ ልጆች በአንድ ቀደም ተብሎ ለሰው ልጆች ሁሉ በተቀመጠ እና በታወቀ የእድገት መስመር እንደሚሄዱ ተደርጎ በመታሰቡ እና እድገታቸውና የሚያሳዩት ለውጥም አንድ-ወጥ (Mechanical) ተደርጎ በመታሰቡ የተነሳ ልጆች በእድገታቸው የሚገጥማቸውን የራሳቸውን ልምድ ግምት ውስጥ ያስገቡ አልነበሩም፡፡ ለረጅም ዘመናት ልጆች ምንም እንኳ የራሳቸው ፍላጎትና የተለያዩ ልምዶችና ቢኖራቸውም፣ ለተሞክሮዎቻቸውም ራሳቸው የሚሰጧቸው ትርጉሞችና አስተያቶች ቢኖሯቸውም ማንም ተገቢውን ክብደት ስላልሰጣቸው ድምጽ-አልባ ሆነው ቆይተዋል፡፡

በዚህ የተነሣም ልጆች ላይ ዘርዘር ያለ እና የእነሱን እውነተኛ ፍላጎት አጉልቶ በማውጣት ዙሪያ የሚያጠነጥን ጥናታዊ ጽሁፍ የማዘጋጀት አስፈላጊነት እይጎላ መጥቷል ፡፡ ከዚህ ቀደም ከላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አብዛኞቹ ጥናቶች በአዋቂዎች ላይ የሚያተኩሩ በመሆናቸው እና ስለ ልጆች የፃፉትም ቢሆን ልጆችን በማህበራዊ መስተጋብርና ሕይወት (Socialization) ውስጥ የሚሰጧቸውን እንደሚቀበሉ ብቻ ተደርገው በመቀረጻቸው የነሱ እውነተኛ ድምጽና ፍላጎት ታፍኖ ቆይቷል፡፡

በሀገራችን እስከ አሁን በልጆች ላይ የተሠሩትን ጥናቶች በማየት በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍል የሚኖሩት ልጆች በከተሞች ውስጥ ከሚኖሩት ጋር በንጽጽር ሲታዩ ብዙም እንዳልተዳሰሱ እንገነዘባለን፡፡ ስለሆነም በገጠር የሚኖሩ ልጆች ስለ ሕይወት ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው፤ ያሏቸውን ተሞክሮዎችና የሕይወት ዕድሎች እና አማራጮች በተመለከተ ብዙ ምርምርና ጥናት ሊደርግ ይገባል፡፡

እንግዲህ ከላይ በማህበራዊ ጥናት መስክ ልጆችን በተመለከተ ያለው ክፍተት ለምን ተፈጠረ? ልጆችስ ለምን እንዲህ ዝቅ ያለ ስፍራ ተሰጣቸው? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ልጆች ለረጅም ዘመናት በሴቶች ላይ እንደሆነው ሁሉ እንደ ጥገኛ ስለሚታዩ፤ አስተሳሰባቸውና ድርጊታቸው በየማኅበረሰባቸው ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ባለመታሰቡም ጭምር ነበረ፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በተለይም ከቅርብ ዘመናት ወዲህ ለምሳሌም በሥርዓተ-ፆታ መስክ እንደታየው ከዚህ ቀደም ድምፃቸው ታፍኖ የነበሩ የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ልምድ፤ እውነተኛ ፍላጎቶችና አስተሳሰቦች እንዲሰሙ በሚደረግበት ግዜ ስለሚኖሩባቸው ማኅበረሰቦች እጅግ የዳበረ እና የተሻለ ሥዕል የሚያሳይ መረጃን ከመስጠታቸው ባሻገር እንደ አንድ የኅብረተሰቡ ክፍሎችም እነዚህ ሰዎች ያሉባቸውን ችግሮችና የሚገጥሟቸውን አዳዲስ ነገሮች በምን ሁኔታ እንደሚወጧቸው ለማየትም ከፍተኛ እድልን ይሰጠናል፡፡

ሌላው ከዚህ በፊት በልጆች ላይ በተደረጉ ጥናቶች እና ልጆችን በተመለከተ በተቀረፁ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ውስጥ አዋቂዎች ስለ ልጆቹ ፍላጎት በደምብ ካለመረዳታቸው ባሻገር ክፍተት ፈጥሮ የነበረው ስለ ልጅነት፤ ስለ ልጆች ባሕሪ እና ፍላጎት በተመራማሪዎች፤ በፖሊሲ አውጪዎችና በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተይዘው የነበሩ ግንዛቤዎች በጣም ጠቅለል ያሉና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ያሉ ልጆች የሚገኙባቸውን የተለያዩ ባሕላዊ፤ ሃይማኖታዊ እና መሰል ሁኔታዎች ግምት ውስጥ አለማስገባታቸው ነበረ፡፡ እውነታውን በምናይበት ግዜ ግን የሰው ልጆች

ልጅነትን የሚያዩበት ሁኔታ እና በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የሚገኙ ልጆች ስለ ራሳቸውና ስለ አካባቢያቸው ብሎም ስለተለያዩ የሚመለከቷቸው ጉዳዮች ያሏቸው አስተሳሰቦች እንደየሚኖሩበት ማኅበረሰብ ባሕልና ወግ የሚለያይ ሆኖ ነው የምናገኘው:: በዚህ የተነሣም የልጆችን ፍላጎቶችና ችግሮች በደምብ አጉልቶ ለማሳየት የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥ የሚገኙ፤ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተከታይ የሆኑ እና በገጠርና በከተማ የሚኖሩ ልጆችን በናሙናነት ወስዶ ንጽጽር ማድረግ ያሻል:: ከዚህ በተጨማሪም ልጆች እንደየ ዕድሜ ክልላቸውና እንደየፆታቸውም የሚያሳዩዋቸው ልዩነቶች የሚኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ በዕድሜ እርከን ያለን የጌታና--ሎሌ ግንኙነት (Patron-client relationship) ብሎም በተዋረድ ያለን ግንኙነት (Hierarchical relationship) በደምብ ለማየት ያስችሉናል:: በፆታም ልጆች የሚያሳዩዋቸው ልዩነቶችና ኅብረተሰቡም ለወንድና ለሴት ልጆች የሚሰጣቸው ግምቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን ሥርዓተ-ፆታዊ አመለካከት አጉልቶ በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል::

## <u>የጥናቱ ዋና ዋና ዓላማዎች</u>

ከላይ የተጠቀሱትን መነሻ በማድረግ እ.ኤ.አ. በ2006/07 የትምህርት ዘመን በሰዊድንና በኖርዌይ የሕፃናት አድን ድርጅቶች እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሶሻል አንትሮፖሎጂ የትምህርት ክፍል ትብብር አምስት የማስትሬት ዲግሪ ተማሪዎችን ያሳተፈ ሰፊ ጥናት በሕፃናት ጉዳይ ላይ ተካሄደ:: ጥናቱ በዋናነት ዓላማው ያደረገው በኢትዮጵያ ያለው ልጆችን የተመለከተ ጥናትና ዳሰሳ ከየት ወደየት እንደተሸጋገረ፤ ልጆችም በጥናት እንዴት እንደተዳሰሱ እና ዛሬም ልጆችን በተመለከተ በኢትዮጵያ በናሙናነት ተመረጡ አንዳንድ በገጠርና በከተማ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለውን አመለካከት ማሳየትን ነው:: ጥናቱ ከዚህ ሌላም ልጆች እርስ በርሳቸው ያላቸውን ግንኙነት፤ ስለ ግንኙነቱ እና ስላሉበት ማኅበራዊ ሁኔታ ያላቸውን ግንዛቤና አስተሳሰብ ለመዳሰስ ይሞክራል:: በሌላ በኩል ልጆች በሚኖሩባቸው የተለያዩ የከተማና የገጠር ማኅበረሰቦች ውስጥ ጎልተው ያሉ እና ለረጅም ግዜ የቆዩ ባሕላዊ አስተሳሰቦችን እና ድርጊቶችን እንዴት በራሳቸው ሁኔታ እንደሚተረጉሙ፤ እንደሚያስፋፉ፤ እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ እነዚህን የቆዩ አስተሳሰቦችና ልምዶች በማይቀበሉበት ግዜ እንደሚቃወሙና ለመለወጥ እንደሚሞክሩም ጭምር ለማሳየት ይረዳል:: በተመረጡት የገጠርና የከተማ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም አንዳንድ የመኖሪያ ስፍራዎችና መንገደሮች ማኅበረሰቡ ስለ ልጆች መብት እንዲሁም ፆታዊ እኩልነት ምን ዓይነት አመለካከት እንዳለው ጥናቱ ለማሳየት ይሞክራል:: እንግዲህ እነዚህን አጠቃላይ ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይዟል፤

- ከዚህ ቀደም ድምፃቸው የታፈነውን ልጆች አሁን በምንገኝበት የዓለማችን ሁኔታ ላይ አምጥቶ ስላላቸው አስተሳሰብና ስለ ማኅበረሰባቸው እሴት ብሎም ስለ ራሳቸው ምን ዓይነት ግምት እንደሚሰጡ በነሱው አንደበት ማሳየት፤

- ልጅነትና ስለ ልጅነት የሚሰጡት ትርጓሜዎች እንዲሁም አስተሳሰቦች በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች፤ ብሔር ብሔረሰቦች እና ክልሎች ዘንድ ያላቸውን ልዩነት በማሳየት ልጆችን በተመለከተ በየማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተለያየ አመለካከት አጉልቶ ማውጣት፤

- ልጆችን በተመለከተ ከዚህ ቀደም ያሉ አስተሳሰቦች ላይ በተለይም ከሥርዓተ-ጾታ እና አዳዲስ መረጃዎች አንፃር እየተመዘገቡ ያሉትን ለውጦች በማሳየት በልጆች መብት ላይ አተኩረው ለሚሰሩ ድርጅቶች ግለሰቦች የተሻለ ሥዕል ማቅረብ፤

- ዓለም ዓቀፉ የሕጻናት መብት ስምምነት (Convention on the Rights of the Child) የየማኅበረሰቡን ቁሣዊ፣ መንፈሳዊ እና ባሕላዊ ሁኔታዎች ግምት ውስጥ እንዴት ሊያስገባ እንደሚችል የሚያሳይ ጠቃሚ መረጃ መስጠት፤

- ከፆታዊ ልዩነት ጋር ተያይዞ ለወንዶችና ለሴቶች በቤት ውስጥ የሚሰጡ የሥራ ድርሻዎች እንዴት እንደሚለያዩ ማሳየት፤

- ልጆችን በተመለከተ በየተለያዩ የሕዝብ መገናኛ ብዙሀን (የግልም የመንግሥትም) የሚቀርቡ የልጆች ፕሮግራም፣ ዜና፣ እና መሰል ዝግጅቶች የቱን ያህል ለልጆች ቅርብ ናቸው? ምን ጉድለትና ጥንካሬዎችስ አሏቸው የሚለውን ማሳየት፤

## የጥናቱ ዘዴዎችና የመረጃ ምንጮች

ይህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከ13-16 ዓመት የሚሆናቸውን እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ልጆችን ከከተማና ከገጠር ቦታዎች በናሙናነት በመምረጥ ረዘም ያሉ ቃለ መጠይቆችን አድርጓል:: በናሙናነት የተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚገኙትም በአማራ፤ በኦሮሚያ፤ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች እና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው:: ከዚህ ሌላም ልጆችን በተመለከተ የሚሠሩ የራዲዮ፤ የቴሌቪዥን እና በጋዜጣ፤ መጽሄት ብሎም በመማሪያ መጻህፍት ስላለው ሁኔታ መረጃ ለማሰባሰብ የተለያዩ የሚዲያ ውጤቶችን በዋቢነት ጥናቱ የተጠቀመ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ ልጆች እና ወላጆች እነዚህን ሚዲያዎች እንዴት እንደሚከታተሏቸው፤ ስለሚቀርቡት ፕሮግራሞችና አቀራረባቸውም ያላቸውን አስተያየቶች በቃለ-መጠይቅ ቀርበዋል:: ከቀጥታ ቃለ-መጠይቅ በተጨማሪም ሰፋ ያሉ እና ተከታታይ የቡድን ውይይቶች (Focus Group Discussions) በናሙናነት በተመረጡትና ከላይ በተጠቀሱት ክልሎችና በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ካሉ ተማሪዎች፣ መምህራን እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወላጆች ጋር ጭምር ተደርገዋል:: በዚህ ጥናት ተሳታፊ የነበሩትና ወደ ተለያዩ ክልሎች የሄዱት አጥኚዎች ራሳቸው እንደ ትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ በአንዳንድ ድርጊቶችና እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌም መምህራንን ተክተው በማስተማር) ተሳታፊ በመሆን (Participant observation) ስለ ተማሪዎቹ ሕይወት ይበልጥ ተዓማኒነት ያለውና ውስጣዊ ሁኔታዎችን የሚያሳይ ስዕል ለማግኘት ሞክረዋል:: በጥናቱ የተሳተፉ አጥኚዎች የየዕለት ማስታወሻ ይይዙ እና በተለያዩ ግዜያት የሚጥሟቸውን ነገሮች በወረቀት ያሰፍሩ የነበረ ሲሆን በቃለ መጠይቆች ወቅትም ፈቃደኝነታቸውን በመጠየቅ ከአብዛኞቹ ተማሪዎችና ወላጆች እንዲሁም መምህራን

ጋር ሲሆኑ ውይይቶችን በመቅረጸ ድምጽ ይቀዱ ነበረ:: አጥኚዎቹ ከዚህ ሌላም ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን እና በተለያዩ ሀገሮች (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ከዚህ በፊት የተሠሩ የዲግሪ ማሟያ ጽሁፎችን፤ መፃህፍትን፤ ጥናታዊ ጽሁፎችን እና የመሳሰሉትን በዋቢነት  እንደ ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭ (Secondary Sources) ተጠቅመዋል::

## የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

### ሀ/ «ጥሩ» እና «መጥፎ» ልጆች በምን ይገለፃሉ?

ተማሪዎች ባጠቃላይ «ጥሩ» የሚሉትን ተማሪ የሚገልፁት የቤት ሥራን በአግባቡና በጊዜ ሰርቶ በመምጣት፣ ባለማርፈድ፣ ባለመቅረት፣ ፀጉርን በማበጠር፣ የመለዮ ልብስ (Uniform) በመልበስ፣ አስተማሪን በማክበር እና ክፍል ውስጥም ባለመረበሽ ነው::

በሌላ በኩል «መጥፎ» የሚሉት ተማሪ አስተማሪዎቹን የማያከብር፣ ክፍል ውስጥ የሚረብሽ፣ ደብተሩን በንጽህና የማይዝ፣ ሌሎችን ተማሪዎች በጉልበት የሚያስፈራራ፣ በተደጋጋሚ ከክፍል የሚባረር እና የሚቀረውን ነው::

ይሁን እንጂ አጥኚዎቹ በገጠርም ሆነ በከተማ በተዘዋወሩባቸው ትምህርት ቤቶች ባካሄዷቸው ቃለ-ምልልስና የራሳቸውም ምልከታ (Observation) እንዳረጋገጡት «ጥሩ» እና «መጥፎ» የሚባሉት አጠራሮች ፆታዊ ልዩነት ነበራቸው:: ለምሳሌም ተማሪዎቹ «መጥፎ ወንድ ተማሪ» እና «መጥፎ ሴት ተማሪ» በሚሏቸው መሀከል ልዩነቶች ነበሩ:: ለአብነት ያህልም መደባደብን ለወንድ ልጅ እንደ መጥፎ እና ተቀባይነት የሌለው ባሕሪ አድርገው ሲያስቀምጡ ሴት ተማሪዎችን «መጥፎ» ብሎ ለመፈረጅ ግን ይህንን አልተጠቀሙም:: በሌላ በኩል ወንድ ልጆች ከትምህርት በኋላ መሸት አድርገውና ቆይተው ወደ ቤታቸው ቢገቡ በፍረጃው ላይ ለውጥ የማያመጣ ሲሆን ሴት ልጅ  ግን መሸት ካደረገች «ዱርዬ»፤ «ባለጌ» እና የመሳሰሉት ቅጽል ስሞች ተሰጥተዋት «መጥፎ» ተብላ ትፈረጃለች:: በሌላ በኩል ወንዱ ተማሪ ከትምህርት ቤት መልስ ወላጆቹን በቤት ውስጥ ስራ ባያግዝ በተለይ በከተሞች አካባቢ ምንም ችግር ያልነበረው ሲሆን በገጠር ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተማሪዎች፤ መምህራንና ወላጆች እንደተስማሙበት ግን ሴቷ ይህንን ባታደርግ «መጥፎ» ትባላለች::

ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች የሚያመላክቱት ተማሪዎቹን «ጥሩ» እና «መጥፎ» ብሎ ለመፈረጅ በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ ጎልተው የነበሩትን ባሕላዊ እሴቶችና አመለካከቶች መሠረት ማድረጋቸውን ነው:: በ«ጥሩ» እና «መጥፎ» ፍረጃዎች መሀከል በተለይም በሁለቱ ፆታዎች የታየው ልዩነት ማኅበረሰቡ ለወንድና ለሴት ልጆች የሚሰጠውን የተለያየ ግምት እንዲሁም ተንሠራፍቶ የቆየውን የወንድ የበላይነትና ትምክህት (Male-dominated Patriarchy) የሚያንጸባርቅ ነበረ::

### ለ/ መብትን በተመለከተ ልጆች ያላቸው ግንዛቤ

በቃለመጠይቆቹ በተለይም በከተሞች ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተገኙ መረጃዎች የሚያሳዩት ወላጆችና ተማሪዎች በሕጻናት መብቶች ድንጋጌው ኮንቬንሽን ላይ የተቀመጡትን መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች በተመለከተ ጥሩ ግንዛቤ እንዳላቸው ነው:: በከተሞች አጥኚዎች በተዘዋወሩባቸው ትምህርት ቤቶች እንደተመለከቱት ተማሪዎች መብቶቻቸውን በተመለከተ ግንዛቤው ስለነበራቸው እነዚህ መብቶቻቸው በሚጣሱበት ግዜ የመቃወም አዝማሚያዎችን (ለምሳሌም አካል ላይ ስቃይ የሚያደርስን የአስተማሪ ቅጣት በመቃወምና አስተማሪውን ለአስተዳደር በሕብረት በማጋለጥ) አሳይተዋል:: በአንጻሩ በገጠር ደግሞ አንዳንድ የተዛቡ አመለካከቶችና ባሕላዊ እሴቶች ፀንተው በመቆየታቸው አንዳንድ ሴት ተማሪዎች በፆታቸው እነሱን የሚያሳንስና የበታች የሚያደርግ አስተያየትና ተግሳጽ ከአስተማሪዎች ሲሰጣቸው ያለ ተቃውሞ ሲቀበሉ ተስተውለዋል:: ባጠቃላይ ለመብት የመቆምና መብትን የማስከበር ነገር በትምህርት ቤቶች ውስጥ ብቻ (ለዚያውም በከተሞች ውስጥ ባሉት) የተወሰነ ነበረ ማለት ይቻላል:: በቤት ውስጥ ምንም እንኳ ወላጆች ስለ መብቶቹ ግንዛቤው ቢኖራቸውም በተግባር የሚያሳዩት ግን የተለየ ነበረ:: ከትምህርት ቤቶች ጋር በንንጽር ሲታዩ መኖሪያ ቤቶች የልጆች መብት ብዙም የማይከበርባቸው ሆነው ተገኝተዋል:: ቤተሰቦች ስለ ልጆቻቸው መብት ቢያውቁም እነዚህን መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማክበሩን ለልጆቻቸው እንደ ማሸነፍ፣ ለነሱ ግን እንደ መሸነፍ አድርገው ስለሚቆጥሩት መብቶቹን መሸራረፉን መርጠዋል::

### ሐ/ መምህራንን ማክበር፣ ምርቃትና፣ ቅጣት

ተማሪዎች መምህራን ወደ ክፍል ሲገቡ ከወንበራቸው ላይ ብድግ ብለው  ይቀበላሉ:: ሆኖም ከዝቅተኛ ክፍሎች ጋር ሲነፃጸር ተማሪዎች በዕድሜና በአካል እያደጉ በሚመጡባቸው ከፍ ያሉ ክፍሎች ውስጥ በተለይም ወደ መጨረሻ አካባቢ የሚቀመጡ ተማሪዎች ዘንድ ይህ ነገር ደብዘዝ እያለ እና እየቀነሰ መጥቷል:: በሌላ በኩል በተለይም ወደ ፊት አካባቢ የሚቀመጡ እና ብዙውን ግዜ በዕድሜ አነስ ያሉ ተማሪዎች ለአስተማሪዎች አቀባበል ሲያደርጉና በራሳቸው ጨርቅ ጭምር ጥቁር ሰሌዳን እና የአስተማሪን ጠረጴዛ ሲያጸዱ ተስተውለዋል:: የቤት ሥራን እና የክፍል ሥራን መስራት ብዙውን ጊዜ እንደታየው ትምህርቱ ስለሚጠይቅና በዚያ ክፍል የሚጠበቅባቸውን የእውቀት ደረጃ ለማግኘት ሳይሆን እንዲያውም ከዚያ በላይ ለአስተማሪው ካላቸው አክብሮትና ወላጆቻቸውን ከመፍራት አንፃር እንደሚሰሩት ተማሪዎች አልሸሸጉም:: ሲቀሩ እና አርፍደው ሲመጡም ቢሆን የሚያመልጣቸው የትምህርት ክፍለ ጊዜ ሳይሆን ለአስተማሪያቸው ያሳዩት ያልተገባ ባሕሪ ነው ጎልቶ የሚታያቸው:: ተማሪዎች ባብዛኛው አስተማሪዎቻቸውን ፊት ለፊት ሲያገኟቸው «አንቱ»፣ «እርስዎ» በማለት ሲጠሯቸውና አክብሮት ሲያሳዩዋቸው ታይተዋል:: ከዚህ ሌላም የሚያከብሯቸውን መምህራን «ጋሼ» ወይንም «እትዬ» (ለሴት መምህራን) ብለው ሲጠሩ ነበረ:: በተማሪዎች ዘንድ መምህራንን «የእውቀት አባት» ወይንም «የቀለም አባት» ብሎ መጥራት የተለመደ ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ተማሪዎች ለመምህራንና ወላጆቻቸው ያላቸው አክብሮትና በሁለቱ መሀከል ያለው የዕድሜና የደረጃ ልዩነት ተማሪዎቹ በአካላቸው በሚያሳዩዋቸው የተለያዩ ምልክቶችና ቋንቋዎችም ጭምር ይገለፃሉ:: በሌላ በኩል ግን መልካም ሥነ-ምግባር የጎደላቸውን (ለምሳሌም የሚጠጡ፣ በመጠጥ ጠረን ክፍሉን የሚያውዱ፣አጉል ስድብ የሚያበዙ ወይንም

በተማሪው ዘንድ የሚጎመዝዝ ቀልድ የሚቀልዱ) መምራንን ተማሪዎች በጣም ዝቅ አድርገው ይመለከቷቸው ነበረ:: በሌላ በኩልም በርካታ ሴት ተ ማሪዎች አንዳንድ ጊዜ ማርክ ለመጨመርና ከክፍል ለማሳለፍ ሲሉ ለፍቅር ግንኙነት የሚጠይቋቸውን አስተማሪዎች በጣም ዝቅ አድርገው ከመመልከታቸውም ባሻገር እነዚህ መምህራን በተማሪ ው ዘንድ ክብርን ያጡ ነበረ::

ወላጆችና መምህራን ጥሩ የሠሩ ተማሪዎችን እና ታታሪ፤ ታዛዥ የሆኑትን በተለያዩ ምርቃቶች ያበ ረታታሉ:: ብዙውን ጊዜም «ጎሽ፤»፣ «ጎበዝ»፣ «በርታ/ በርቺ» ወዘተ. የተሰኙት ለእነዚህ ተማሪዎች ይሰጣሉ:: ከዚህ ሌላም ለማበረታታት የቁሳቁስ ስጦታ ዎች በተለይም በወላጆች (አንዳንዴም ደግሞ በትምህርት ቤቱ አስተዳደር) የሚሰጡባቸው ሁኔታ ዎች አሉ::

ቅጣትን በተመለከተ ተማሪዎች በቃለ መጠይቁ እንዳረጋገጡት አካል ላይ ጉዳት የማያደርስ እስከሆነ ድረስ ተማሪዎችን ለመግራት እንደ ቁንጥጫ፣ በአርጩሜ ዠለጥ ማድረግ ያሉት አስፈላጊ ናቸው ብለው ያምናሉ:: ሆኖም ሌሎችን ለምሳሌም ራሳቸውን መምታት፣ ማንበርከክ፣ በዱላ በኃይል መምታት፣ ሽንት ቤት ማስጠረግ (ለሴቶች)፣ ጉድጓድ ማስቆፈር (ለወንዶች) የመሳሰሉት በጣም የሚበዙ እና ተማሪ ዎች ላጠፏቸው ጥፋቶች የማይመጥኑ እንደሆኑ ስለሚቆጥሯቸው በነዚህ ላይ ተቃውሞ ነበራቸው:: ብዙውን ጊዜ እንደታየው ትምህርት ቤቶች ለየጥፋቱ ያስቀመጧቸው የቅጣት ዓይነቶች ስለነበሩ እና እነዚህም የማይለዋወጡ በመሆናቸው ተማሪዎች እነዚህን ቅጣቶች በጣም የከፉ አድርገው ይቆጥሯቸዋል:: የቅጣቶቹ መጥበቅና ክብደትም ተ ማሪዎቹ ለአስተማሪዎቻቸው ፍርሃት እንዲያድርባቸው ሲያደርጉ የተስተዋሉባቸው በርካታ አጋጣሚዎች በጥናቱ ተጠቅሰዋል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ግን የቅጣቶቹ መክበድና ከመምህራኑ የሚታዩ ጭካኔ የተሞላባቸው አንዳንድ የቅጣት ድርጊቶች ተማሪዎችን ወደ ትክክለኛውና ጥሩው ባሕሪ ከመመለስ ይልቅ በተ ቃራኒው ይበልጥ የማይታዘዙ የማድረግ ያልተፈለገ ውጤት እንደነበራቸው በጥናቱ ተመልክቷል::

በቃለ-መጠይቁ ጊዜ ተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም ወላጆች አክብሮት፤ ምርቃትና ቅጣትን በተ መለከተ የሰጧቸው አስተያየቶች በማህበረሰቡ ውስጥ በዕድሜ እና በደረጃ ያሉ ልዩነቶችን መሠረት በማድ ረግ ግንኙነቶች እንዴት መሆን እንዳለባቸው ለረጅም ግዜ ተይዞ የነበረውን ግንዛቤ የሚያንፀባርቁ ናቸው:: ባብዛኛውም ተማሪዎችና አስተማሪዎች በደረጃ ተዋ ረድ ያለን ልዩነት መሠረት ያደረገ (Hierarchical) እንዲሁም የጌታና የሎሌ--መሰል (Patron-client) ግንኙነት ተስተውሎባቸዋል::

## መ/ ወንድና ሴት ተማሪዎች በትምህርት ቤት

በጨዋታ ግዜ ወንድ ተማሪዎች በገጠርም ሆነ በከተ ማ እንደታየው በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ሰፋ ያለ ቦታን ይዞ የመጫወት፤ የመዝለል፤ በፍጥነት የመሮጥና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የመዘዋወር ባሕሪ አሳይተዋል:: በተቃራኒው ሴት ተማሪዎች በሚጫወቱበት ጊዜ ከወንዶቹ ጋር በንጽጽር ሲታይ አነስ ያለ ቦታን የመያዝ፤ ብዙ ያለመዝለል እና በትናንሽ ቡድኖች የመወሰን ባሕሪን አሳይተዋል::

ገጠር ውስጥ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች በክፍል ውስጥ ባሉ የወንድ እና የሴት አለቆች ላይ ተማሪዎች የተለያዩ ስሜቶችን አንፀባርቀዋል:: ከወንድ አለቃ ጋር ሲነፃፀር ሴቶችን ያለ መፍራትና ያለመታዘዝም ተስተ ውሏል:: በአንዳንድ ቃለ-መጠይቆችም ሴቶች ገና ለዚህ ደረጃ እንዳልበቁና ዓለቃ ቢሆኑ ክፍሉን ያስደፍራሉ የሚሉ አመለካከቶች ተንጸባርቀዋል:: በከተሞች አካባቢ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ግን ሴቶች ከሞላ ጎደል ከወንድ እኩዮቻቸው ባልተናነሰ በእልቅናቸው ሲፈሩ፤ ሲከበሩ እና እኩል ቦታ ሲሰጣቸው ታይቷል::

ሴት ተማሪዎች በተለይም በገጠር ጎበዝና በክፍሉ በሚያደርጉት የክፍል ተሳትፎ የታወቁ የሚበረታቱ ቢሆኑም እንኳ ካልተጠየቁ በቀር ብዙም ደፍረው በራሳቸው ጥያቄ ለመመለስ ይቸገራሉ:: በሌላ በኩል በከተማም ሆነ በገጠር እንደታየው ሴቶች መልስ ሲመልሱም ሆነ ሲናገሩ አፋቸውን በእጃቸው የመሸፈን እና ትንሽ የማቀርቀር ባሕሪ ተስተውሎባቸዋል:: በትምህርት ቤት ውስጥ ሴትና ወንድ ብዙም ጓደኛ ሞች ሲሆኑ አይስተዋልም:: በተለይም ከፍ ባሉት ክፍሎች የሚገኙ ተማሪዎች ውስጥ የሚፈጠሩ የጓደኝነት ቁርኝቶች የጾታ ስብጥር አይታይባቸውም ማለት ይቻላል:: ይህም በወንድና በሴት መሀከል ለሚደረግ ንፁህ የትምህርት ቤት ጓደኝነት ሳይቀር ባብዛኛው ተማሪው በሌላ ማለትም በፍቅር ተዋደው እንደተገናኙ አድርጎ የመመልከት ወይንም የማውራትና የማስወራት አዝማሚያ ስላለው ያንን ከመፍራት የመጣ ነው::

## ሠ/ አንዳንድ ተማሪዎች ተንሰራፍቶ የቆየውን ባሕላዊ አመለካከት ስለመዋጋታቸው

በጥናቱ እንደታየው ሁሉም ተማሪዎች በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ተንሰራፍቶ የቆየውን እና እነሱ የማይቀበሉትን አመለካከት ታግሰው፤ ሁል ጊዜም ተ ገዢ ሆነው አልቆዩም:: አንዳንዶቹ ከራሳቸው ሁኔታ ጋር እያመሳሰሉ ሊለውጡት ሲሞክሩ ሌሎች ደግሞ ተቃውመውታል:: ይህ ዓይነቱ ባሕሪ ልጆች ቀደም ሲል በተለያዩ በአዋቂዎች ስለ ልጆች በተሠሩ ጥናቶች የሚሰጧቸውን የሚቀበሉ (Passive) አድርጎ ከመመልከት ይልቅ በራሳቸውም ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ (Active Agents) መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ለየት ባለ መልኩ ለመመልከትም ይረዳል:: በከተሞች ውስጥ ባሉት ትምህርት ቤቶች ተ ማሪዎች ካሉበት ማኅበረሰብ አመለካከት ለየት ያለን ነገር በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አራምደዋል:: አንዳንድ ተ ማሪዎች ብድግ ብሎ አስተማሪ መቀበልን «አላስፈላጊ» ብለውታል:: ሌሎች ደግሞ በስፋት ወንድና ሴት መሀከል መቀራረብ እንደ ነውር በሚታይበት ሁኔታ ያንን በመቀልበስ ፆታዊ ስብጥር የሚታይበት ቡድናዊ ጓደኝነት ፈጥረዋል::

ከዚህ በተለየ ግን በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎችም ቢሆን ተማሪዎች የራሳቸውን ተነሳሽነት በመውሰድ ጾታዊ ልዩነትን መሠረት አድርገው ባቋቋሟቸው ኮሚቴዎች ሌሎች ችግሮችን ለማሸነፍ ሞክረዋል:: ለምሳሌም በአማራው ክልል በምሥራቅ ጎጃም ዞን ውስጥ የነበሩ አንዳንድ መሰል ኮሚየሚፈጠሩ እና ዎች በቤት ውስጥ ከልክ ያለፈ የሥራ ጫና የሚያ ረግባቸውን ሴቶች ተከታትለው ጫናቸው እንዲቀንስ አድርገዋል:: በተመሣሣይም አንዳንድ ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዳይከታተሉ እንቅፋት የሆነባቸውን የልጅነት ጋብቻ (Early Marriage) በመከላከል ዘንድ ኮሚቴዎቹ ትልቅ ሥራ መስራታቸውን ጥናቱ ጠቁሟል::

## ረ/ በገጠርና በከተሞች ውስጥ በሚገኙ ተማሪዎች መሀከል የተስተዋሉ ልዩነቶች

- በገጠር የሚገኙ ልጆች ትምህርት ቤት ሄደው የመማርና በቤት ውስጥ ከባድ ሥራን የመሥራትን ጣምራ ኃላፊነት ሲሸከሙ በከተሞች ግን ይህ ብዙ አይስተዋልም፤
- በከተሞች የሚገኙ ልጆች ብዙውን ጊዜ በእንክብካቤ ይያዛሉ፤ ይህም ቤተሰቦቻቸው ባብዛኛው ለዘመናዊ ሕይወትና አዳዲስ መረጃ ይበልጥ ቅርበት ያላቸው ስለሆኑ ነው፤
- በገጠር የሚገኙ ልጆች ገና በለጋ ዕድሜያቸው ሥራ ይሠራሉ፤
- በገጠር ያሉ ልጆች ከከተማ አቻዎቻቸው ጋር ሲነፃፀሩ አፈር ይላሉ፤ ይህም ለዘመናዊው አኗኗር ያላቸው ቅርበት ውሱን በመሆኑ ነው፤
- በከተማ የሚገኙ ልጆች ስለ ሕጻናት መብቶች ይበልጥ ሰፋ ያለ እና ጥሩ ግንዛቤ አላቸው፤ ለዚህም የሚኒ ሚዲያ እና አንዳንድ የተማሪ ኮሚቲዎች መስፋፋት ብሎም ተማሪዎቹ ለተለያዩ ሚዲያዎች ያሉዋቸው ቅርበት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል::

## ሰ/ ልጆችና ሚዲያ

ጥናቱ ለናሙናነት የመረጣቸው የመንግሥት እና የግል የፅሁፍ ሚዲያዎች ዕለታዊው *አዲስ ዘመን*፤ የእንግሊዝኛው *Ethiopian Herald*፤ በሳምንት ሁለት ግዜ የሚወጣው *ሪፖርተር* እና እንግሊዝኛው *The Reporter*፣ እንዲሁም በሳምንት አንድ ጊዜ ታትሞ ለንባብ የሚበቃው *አዲስ አድማስ* ጋዜጦች ናቸው:: በጥናቱ እንደታየው ከመንግሥት ጋዜጦች ጋር ሲወዳደር በግል ጋዜጦች ላይ ስለ ልጆች የሚቀርቡ ነገሮች ብዙም የተለመዱ አይደሉም:: ለዚህም አዘጋጆቹ የተሻለ ሽያጭ እና ገቢ ለማግኘት አዋቂዎችን የተመለከቱ ፖለቲካ፣ ፍቅር እና መሰል ጉዳዮች ላይ ማተኮር ስለሚመርጡ ነው ተብሏል:: ይህም ሆኖ በሁለቱም ጋዜጦች ላይ ልጆችን የተመለከቱ የተለያዩ ጽሁፎች ይነስም ይብዛም መውጣታቸው የታወቀ ቢሆንም በጥናቱ የተካፈሉ ልጆች ግን ጋዜጦችን አግኝተው ለማንበብ ችግር ስላላቸው ባብዛኛው ስለ ልጆች የሚፃፈውን እንደማያነቡ ነው የገለፁት::

የኤሌክትሮኒክ ሚዲያውን በተመለከተ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና በራዲዮ ኢትዮጵያ፤ ራዲዮ ፋና እና ኤፍ. ኤም. 97.1 ላይ አተኩረው የተደረጉ ቃለ-ምልልሶች እንዳሳዩት ልጆች ምንም እንኳ ሳምንታዊ የሆኑ እነሱን የተመለከቱ ዝግጅቶች ቢኖሩም ከእነዚህ ይልቅ አዋቂን የተመለከቱ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ለምሳሌም ድራማን እና ቀደም ሲል በወቅቱ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ይተላለፍ የነበረውን «ኢትዮጵያን አይዶል ሾው» የመሳሰሉ ፕሮግራሞች መከታተል የበለጠ ያስደስታቸው እንደነበረ ተናግረዋል:: የቴሌቪዥን ፕሮግራም በደምብ ከሚከታተሉት ልጆች መሀከል አብዛኞቹ በወቅቱ ይተላለፍ የነበረውን የአባባ ተስፋዬን «ተረት ተረት» ይበልጥ ይወዱት እንደነበረ ገልጸዋል:: ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ላይ የሚቀርቡትን የልጆች ፕሮግራሞች የማይከታተሉ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ልጆች፤ «እነዚህን ፕሮግራሞች መከታተል ሲበዛ ሕጻን ያደርገናል» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል::

በሚዲያዎቹ ውስጥ ፆታዎችን በተመለከተ ሁለቱንም ፆታ እንደ አስፈላጊነቱ የማካተትም ሆነ ጾታዊ እኩልነትን በማንፀባረቅ ረገድ ጥሩ ስራ ተሰርቷል:: ይሁንና አንዳንድ ጊዜ በቋንቋ እና በተወሰኑ ይዘቶች ከዚህ ቀደም ፆታዊ አድልዖዎችን ያሳዩ የነበሩ አንዳንድ አባባሎችን ሲጠቀሙ ተስተውለዋል:: በሌላ በኩል ሃይማኖታዊ በዓሎችን እና የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች አለባበሶችን፣ ባሕሎችን እና ጭፈራዎችንም በፕሮግራማቸው አካትተው ለማቅረብ ሞክረዋል:: ሆኖም በአብዛኛው የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችን በማካተቱ ዘርፍ ድክመቶችም ታይተዋል:: ይህ ድክመት በክርስትና እምነት በሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች ያሉትን በማካተቱም ረገድ እንደታየ ጥናቱ ጠቁሟል::

## የማጠቃለያ ሀሳቦች

በጥናቱ እንደታየው ልጆች ከቤት ጀምሮ ይዘውት የመጡትን ታላላቆችን እና በደረጃ የሚበልጧቸውን የማክበር ባሕሪ ትምህርት ቤት ውስጥም አንጸባርቀውታል:: በዚህ ረገድ ለአስተማሪዎቻቸው፤ ለዳይሬክተሮችና ለክፍል አለቆችም አክብሮት አሳይተዋል:: በተማሪዎችና በመምህራን መሀከል ያለው ግንኙነት የጌታና ሎሌ---መሰል እንዲሆን ትምህርት ቤቶችም ባወጧቸው የውስጥ ደምቦች እንዲሁም በተግባር በሚያደርጓቸው ነገሮች አስተዋፅዖ አድርገዋል::

በሌላ በኩልም በማኅበረሰቡ ውስጥ ተስፋፍቶ የቆየው ለሴቶች የሚሰጥ ዝቅ ያለ ግምት እና የወንድ የበላይነትን ተገን ያደረገ ትምክህት (Male-dominated Patriarchy) በትምህርት ቤቶች ውስጥም ቀጥሎ ታይቷል:: ተማሪዎችም ባብዛኛው ይህንን ተንሰራፍቶ የቆየውን ባሕል የሚያጠናክር ግንኙነት አሳይተዋል::

ስለ ሕጻናት መብቶች ከገጠር ቦታዎች ጋር በንጽጽር ሲታይ በከተሞች ውስጥ ወላጆችና ልጆች የተሻለ ግንዛቤ ቢኖራቸውም በተግባር ግን እነዚህ በከተማ የሚገኙ ወላጆች ለልጆቻቸው እነዚህን ሁሉ መብቶች ማክበርን እንደ መሸነፍ አድርገው በመቁጠራቸው መብቶቹን ይሸራርፏቸዋል:: ቁጥራቸው ቀላል በማይባሉ በጥናቱ በተካተቱ ቤተሰቦች እንደታየው ደግሞ ልጆቹ ራሳቸው መብት ብለው የሚቆጥሯቸው ቤተሰቦቻቸው በፈቃዳቸው የሚሰጧቸውን ነገሮች ብቻ ነው::

ይሁን እንጂ ተማሪዎች እነዚህን ሁሉ ተንሰራፍተው የቆዩ ፆታዊ እና የጌታ--ሎሌ መሰል ግንኙነቶች በተወሰነ መልኩ ለመቀየር የሞከሩባቸው ሁኔታዎች ነበሩ:: ተማሪዎች ምንም እንኳ መምህራንን የማክበርና የመታዘዝ ግዴታ እንዳለባቸው ቢያውቁም መብታቸውን የሚዳፈሩትን እና ለአስተማሪ ያልተገባ ነው ብለው የሚያስቡትን ባሕሪ የሚያሳዩዋቸውን መምህራን ክብር ሲነፍጉ በጥናቱ ታይቷል:: ከዚህ ሌላም አንዳንድ ተማሪዎች (በተለይም በከተማ ያሉት) ከበድ ያሉ ቅጣቶችን የተቃወሙባቸው ሁኔታዎች አሉ:: ፆታዊ ስብጥር በማይታይባቸው እና ወንድና ሴት ተማሪዎች መቀራረብን እንደ ነውር በሚቆጥሩባቸው አካባቢዎች የተወሰኑ ተማሪዎች የቅርርቡን ነውርነት እንዳላመኑበት በቃለ መጠይቅ ያረጋገጡ ሲሆን በተግባርም አጥኚዎች ከዚህ የተለየ ቁርኝት ከተቃራኒ ፆታ ጋር

ሲፈጥሩ አስተውለዋል፡፡

ልጆችን በተመለከተ በህትመትና በኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎች የሚቀርቡ ነገሮች አስደሳች፤ ማራኪ እና የልጆችን ችግር የሚዳስሱ ነገሮችን ቢያካትቱም በማህበረሰቡ ውስጥ የቆዩ አንዳንድ ፆታዊ አድልዖዎችን መሠረት ያደረጉ አገላለፆችን ይጠቀማሉ፡፡ ከዚህ ሌላም ልጆችን እንደተቀባይ ብቻ አድርጎ የማየት ነገሮች አሉ፡፡ በጥናቱ የተሳተፉ ልጆች በቃለ መጠይቅ የልጆች ፕሮግራምን መከታተል ከሚገባው በላይ ሕጻን የሚያደርግ እንደሚመስላቸውና ይልቅ ለአዋቂዎች የተዘጋጁ እንደ ድራማ የመሳሰሉትን ዝግጅቶች መከታተልን እንደሚመርጡ አስታውቀዋል፡፡ ከመንግሥት ሚዲያ ጋር ሲተያይ በግሉ የሚዲያ ዘርፍ ስለ ልጆች የሚጻፈውና የሚዘገበው በጣም አናሳ ሆኖም ተገኝቷል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ እንግዲህ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆቻቸው ለተለያዩ ዘመናዊ መረጃዎች፤ አስተሳሰቦችና አዳዲስ ነገሮች ቅርብ በመሆናቸው የነሱን ፈለግ ተከትለው የቆዩ አስተሳሰቦችን እና ባሕላዊ እሴቶችን ባላመኑባቸው ጊዜ ለመቀየር የተሻለ ድፍረትን አሳይተዋል፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ሁኔታም በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰጡ እንደ ሲቪክስን የመሳሰሉ ትምህርቶችና የሚኒ ሚዲያ ክለቦች እንዲሁም አንዳንድ ችግር አስወጋጅ ኮሚቴዎች ከፍተኛ አስተዋፆ አድርገዋል፡፡ ይህም ቢሆን ግን ተማሪዎች በከተማም ቢሆን ባብዛኛው ተንሰራፍቶ የቆየውን ባሕል በራሳቸው መንገድ ማራመድ እንጂ ሙሉ በሙሉ መለወጥ ግን እንዳልቻሉ መደምደም ይቻላል፡፡ በተቃራኒው በገጠር በተዳሰሱት ለናሙናነት በተመረጡ ቦታዎች እንደታየው ተማሪዎች በቤት ውስጥ ስራ ስለሚጠመዱ በትምህርታቸው ወደ ኋላ ለመቅረት አንዳንዴም ለማቋረጥ ተገደዋል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሴት ተማሪዎች ቁጥር ገጠር በሚገኙ ትምህርት ቤቶችም በከፍተኛ ሁኔታ ቢያሻቅብም ሴቶች ግን ባለባቸው የባህል ተጽዕኖዎች ምክንያት በከተማ ከሚገኙ የፆታ አቻዎቻቸው በተነፃፃሪነት ሲታዩ በሚገጥሟቸው ችግሮችና የዕለት ተዕለት ፈተናዎች ላይ ትርጉም ያለው ተቃውሞ ማሰማት አልቻሉም፡፡

## የፖሊሲ ጠቋሚ ሀሳቦች

ከዚህ በኋላ ለወደፊቱ በልጆች ዙሪያ የሚነደፉ ፕሮጀክቶችና ፖሊሲዎች በተቻለ መጠን የልጆችን መብት ግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ ሌላ ወላጆች ልጆቻቸውን ስላለባቸው ግዴታዎች ብቻ በማንሳት ግዴታ ከሚጥሉባቸው ይልቅ ስለ መብቶቻቸውም ሊነግሯቸውና ሊያስተምሯቸው፤ እነሱም መብቶቹን ሊያምኑባቸው ይገባል፡፡

የልጆችን መብት ለማስከበር የሚደረጉ ማንኛቸውም ጥረቶችና እንቅስቃሴዎች ስለ ልጆች በተለያዩ የሃይማኖት፤ የብሔርና ባህላዊ አስተሳሰቦችን ከግምት ውስጥ ያስገቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ከዚህም ሌላ ልጆች በዓለም ዓቀፉ የሕጻናት መብት የተጎናጸፏቸውን መብቶች ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ልጆች በሚመለከቷቸው ጉዳዮች ላይ የሚሰጧቸውን ተቀባይ ብቻ ሳይሆን ንቁ ተሳታፊ እና ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉም ጭምር ተደርገው ሊታሰቡ ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ልጆች በማናቸውም እነሱን በተመለከተ በሚወጡ ፖሊሲዎች ላይ ድምጻቸው ሊሰማ እና ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡

በገጠር በሚገኙ ተማሪዎች በተለይም በሴቶች ላይ በቤት ውስጥ የሥራ ጫና እጅግ በጣም የበዛ በመሆኑ በፆታ እኩልነት እና አንዳንድ ጎጂ ባሕሎች ላይ ግንዛቤን የማሳደግ ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በገጠሪቱ የኢትዮጵያ ክፍሎች ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን ለመኖሪያ ቅርብ ሆነው ቢሰሩ ሴት ተማሪዎች ካለባቸው የቤት ውስጥ የሥራ ጫና በተጨማሪ ረጅም መንገድ ከመጓዝ ይድናሉ፡፡

በትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ክለቦችና ኮሚቴዎች የተማሪዎችን መብትና ጥቅሞች በይበልጥ ስኬታማ ሆነው ማስጠበቅ ይችሉ ዘንድ የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ ሊቸራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም በዓለም ዓቀፉ የሕጻናት መብቶች ድንጋጌ የታቀፉትን የተለያዩ መብቶች በተመለከተ በገጠር ያለው ግንዛቤ አናሳ ስለሆነ ቢቻል በቀበሌ ደረጃ የመረጃ ማዕከሎች ተሠርተው ማስተማርና መብቶች ተጥሰው በሚገኙ ጊዜም መፍትሔ ወደሚሰጥ አካል በቀጥታ መምራት እንዲችሉ መደረግ አለበት፡፡

ወጣት ልጆች ለለውጥ እንዳይነሳሱ እንቅፋት የሆኑባቸውን አንዳንድ ባህላዊ አስተሳሰቦች ቀስ በቀስ ማጥፋት ይቻል ዘንድ በሕትመት እና ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ብሎም በትምህርት መፃህፍት ዝግጅት ሥራዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አሳታሚዎች፤ አዘጋጆችና ደራሲያን ስለ ኋላቀር አስተሳሰቦች ጎጂነት ይበልጥ ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

**(ቢንያም ዓለማየሁ)**

**ምንጭ፡-** Eva Poluha, ed. 2007. *The World of Girls and Boys in Rural and Urban Ethiopia*. Addis Ababa: FSS.

**ምስጋናና ማሳሰቢያ**

**ይህ ሰነድ የታተመው በአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የአውሮፓን ሕብረት አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጐ መወሰድ የለበትም፡፡**

**አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**
**ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79**
**ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et**